ስለ ጋዜጠኞቹና ጦማሪያን የፍትሕ ጉዳይ

ከጠበቃ አምሐ መኮንን ጋር



በ1985 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሕግ ተመርቀው እንደጨጡ ልዩ ስቃቢ ሕግ መምሪያ ቤት ለስድስት ወር ያህል ሰርተዋል። በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትር ወስጥ ከ 1986 እስከ 1997 ድተሰዎ የኃላፊነት ደረጃ አገልገለዋል። ከ1997 ጀምሳ በጥበቅናና በማማከር ሥራ ተሰማርተው ይገኛሉ። በተጨማሪም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወዝቲና በቅድስት ማርያም ኮሌጅ በሕግ መምህርነት ለስድስት ዓመት አስተምረዋል። በቅርቡ መንግሥት ያሰራቸው ጋዜጠኞችና ጦማሪያን ጠበቃ ናቸው። ጉዳዩን በተመለከተ ከጠበቃ አምሐ መኮንን ጋር ተነጋግረናል።

በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች ከጠበቃቸው ጋር መገናኘት የሚደምሩት ከመቼ ደምር ነው?

ነክ የተሠመረተባቸው ቤትች ሁሉ ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው። ምክንያቱም በተከሰሩበት ጉዳይ ስለሚሉበት ቃል ከጠበቃቸው ጋር እየተማከሩ መሆን አለበት። በመሠረቱ እንድ ተከሳሪ የተከሳሽነቱን ቃል አልሰጥም ማለት ይችላል። ግን ይህንን ሊያውት የሚችለው ተከሳሪው ከጠበቃው ጋር ሲነጋገር ብቻ ነው።

እንደ ተከሳሪ ከተያዘ ደምር ጀሕን የተረቀደበት መብት ምንድነው?

መደብደብ የለበትም። በተጨማሪም ማንኛውም ተፅዕኖ ሊደርስበትም አይገባም። ይህንን ሁሉ መብቱን ሊያውት የሚችለው ተከሳሪው ከጠበቃው ጋር ሲኖርና ነው። ስለዚህ በኔ አረዳድ እንድ ሰው ከተያዘበት ጀምር ከጠበቃው ጋር የመገናኘት መብት አለው። ይሄንን በተመለከተ የሀገራችን ሕጎች የሚደግፉት ሲሆን ዓለም ዐቀፍ የሕግ ድንጋጌዎች ላይ በጉልህ የተቀመጠ ነው።

እርስዎ በእስር ላይ የሚገኙት ጋዜጠኞችና ጦማሪያን ጠበቃ ነዎት። ስምንደነው ታዲያ ከደንበኞችዎ ጋር እንዲገናኙ ያልተረቀደደዎ?

ይሄ ስምን ሆን በተጥቶ ሊመልስ የሚችለው አድራጊው ክፍል ነው። በመጀመሪያ ተከሳሪዎቹ በተያዙ በ48 ሰዓት ውስጥ ፖሊስ ፍርድ ቤት ማቅረቡ ሕጉን እንደተጠበረ ተሰምቶኛል። ከዚህ በኋላ ያለው ሂደት ግን አንደኛ ፍርድ ቤቱ ከመዝገቡ በፊት ሕጉ እያለ በፖሊስ በኩል ተከሳሪዎቹን ከቤተሰቦቻቸውና ከጠበቆቻቸው እንዳይገናኙ ከልክሏል። ይሄ ሕግን የሚጣረስ ነው። ከዚያ በኋላ ማታዘያ 29 እና 30 ፍርድ ቤት ቀረብን ይሄንን ችግር በማስረዳታችን ፍርድ ቤቱ ቢልጎንሉት ተከሳሪዎች ከጠበቆቻቸው ጋር የመገናኘት ሕገ-መንግሥታዊ መብት እንዳላቸውና ፖሊስ በማናቸውም ሁኔታ ሊከለክል እንደማይገባ በተጣይ ሂደቶችም እኛ ጠበቆች ደንበኞቻችንን ማግኘት እንድንችልና እንዲመቻች ጫናው ከፍተኛ ስለነበሩ መርማሪዎች ትዕዛዝ ሰጥተዋል። በጠዛራችን ላይ ፖሊስም አንድ ተከሳሪ ይሄ መብት እንዳለው ያምናል።

ደሄ በመሆኑ ምንደነው የተሰማዎት?

ሕግ እንዲጣበር ትልቅ ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም እንዲህ ዓይነት ያልተገባ ነገር መፍጠሩ ከፍተኛ ቅሬታና ሥጋትም ፈጥሮብኛል። በወንጀል መከርከር ምንም ችግር የለውም። ፖሊስም ወንጀልን የማጋለጥና ለፍርድ እንዲቀርቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ስለሁ እንደ ዜጋ መተባበር ባለብን ሰዓት መተባበር ግዴታችን ነው። ከዚሁ አኑል አሁን ባለንበት በሙን ተከሳሽ (የተጠረጠረ ሰው) እኑል ተወዳዳሪ የሆኑ መብቶች አሉት። እነዚህም መቅበር መቻል አለባቸው። እነዚህን መብቶች ባለማክበር ምንም አሳማኝ ምክንያት ሊሠጥ አይገባም። ስለዚህ እነዚህ ልጆች ተጠርጣሪዎች ስለሆኑ ነገ ነክ ሲመሠረትባቸው ወይም ላይመሰረትባቸው ይችላል። ተመስርቶባቸውም ነፃ ሊወጡ ስለሚችሉ ይሄ ሁሉ ታሳቢ መደረግ አለበት። ግን አብቃላይ ውጤቱ ሀገርንም መንግሥትም የሚጎዳ ነው።

ትልቁ የፍትሕ ጽኑዕ ዳኝነት ነው። መንግሥት በተወሰኑ ዜጎች ላይ የመብት ገፃነት ማድረጉ ስገባብ ነው?

ዜጎች ሁሉ በሕግ ፊት እኑል ናቸው የሚለው የሕገ-መንግሥታችንም የነባር ሕጎቻችንም መርህ ነው። አንድ በእስር ያለ ሰው ከጠበቃው፣ ከቤተሰቡ፣ ከሃይማኖት አባቱና ከሌሎሙ ጋ የመገናኘት መብት አለው። ፖሊስ መጀመሪያ ሕጉ ተቀምጦ ሕጉን አለማክበሩ ቀጥሎም ፍርድ ቤት አገበ፣ አያለ የፍርድ ቤት ትዕዛዝን አለማክበሩ በአኔ በኩል ጉዳዩን ለሚሰሙ የኔቢረተሰብ ክፍል ትልቅ የደህንነት ስሜት የማጣትና ሌሕን የበላይነት ያለው እምነት የመነጫት ስሜት ይፈጥራል።

ክልንደ ታሪማ መረዳ ለማግኘት የገደ ወደ ኃይል እርምጃ መክፍ አለበት?

ይሄ ጥያቄ በተለይ በሚያገሀ 30 ተጠር ከቀረቡት ተጠርጣሪዎች መካከል በፍቃዱ ኃይሌና አቤል ዋበላ ከገለጹት ጋር የተያያዘ ይመስለኛል። የታሰረን ሰው ማስቀየት፣ ማዋከብ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት የተከለከ ነው። የትኛውም ሀገር የታሰረን ሰው መደብደብ፣ ማዋከብ አይቻልም የሚል ሕግ ሳይኖረውም እንኳን በዚህ ሕግ ይጣል፣ ዓለምም የተስማማበት ነው። አንድ ሰው ከውጪ ዓለም ጋር ሳይገናኝ የሚታሰር ከሆነ በተከከል የሚታሰቡበት ተጠርጣሪውን እያሰቃዩ አፍገረቶ መረጃ ለማግኘት ታስቦል የሚል ደምዳሜ ላይ ነው የሚጠበደው። ስለዚህም በዚህ ሁኔታ ውስጥ የታሰረ ሰው ዕድሉን እግኙቶ ስለመደብደቡ ወይም ስቃይ የደረሰበት መሆኑን ቢናገር ከሰውነቱ ላይ ጭረት አለመኖሩና አለማሰከሉ አልተደበደበም እያስብለውም።

ፖሊስ መረዳ ላይ ስለበበብ ማሰራ ተገቢ ነው? ስንደ ሰው ተጠርጥር ስለስር የሚደበቃው ምን ሊገኝ ነው?

እንግዲህ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓታችን ሕግ የሚለው አንድ ሰው በፍርድ ቤት ትዕዛዝም ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝም ሊያዝ ይችላል። በፖሊስ መዋሪያም ሊጠራ ይችላል። ሕጉ የሚለው ያ ሰው ወንጀል ፈፅሞ ይሆናል ብሎ ስማመን የሚያስችል ከተራ ጥርጣሬ ያለፈና ሁላችንም የምንስማማበት መነሻ ያስፈልጋል። ይሄ መነሻ ደግሞ በአንድ ሰው ቁመና፣ በአንድ ሰው መልክና በአንድ ሰው የኢኮኖሚ አቅም ብቻ በሚኖት የምትደርስበት ድምዳሜ አይደለም። መጀመሪያ የግድ በቂ ማስረጃ መሰብሰብ አለበት። በእኔ እምነት ከማሣሽ በላይ ማስረጃ መሰብሰብ አለበት።

እንደ ጠበቃ እያንዳንዱን መረዳ ስማግኘት ከደንበኞች ጋር መነጋገር ያስበት ይመስለኛል። እርስዎ ከደ ደንበኛዎ ጋር ሄደው እነሱን ማገኘትና ከእነሱ መረዳ መሰብሰብ አስመቻልም በምሪዎ ላይ እንቅፋት አልፈጠረብዎም?

በጣም ትልቅ እንቅፋት ፈጥሯል። ይህን እኛ ብቻ ሳንሆን ፍርድ ቤቱም ተገንዝቦታል። እኛ አስተድመን ልጆቹን አግኝተን ቢሆን በምን ጉዳይ እንደተጠረጠሩ አውቀን፣ እስከሁን ድረስ ምን ዓይነት ምርመራ እየተደረገ መሆኑን፣ አያያዙ እንዴት እንደሚደረ ተረድተን ከፖሊስ ጋር ተወዳዳሪ ሙግት ለማቅረብ የተጠርጣሪውን መብት ስማስከበር ይጠቅማል። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹን በአጃ አድርጎ የፈለገውን ጊዜ መስደ ምናልባትም የፈለገውን የምርመራ ዘዴ ተጠቅሞ አገኘሁ የሚለውን ውጤቶች ደዛ ለሚጠይቀው ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ሊያስገኝለት የሚችል ዓይነት ነው ደዛ የሚቀርበው። እኛ እንደጠበቃ በሕግ መከከለት የሚገባንን አገልግሎት እንዳንሰጥ እንቅፋት ሆኗል። ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝና የውሳኔ ጥራት ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም።

አንዲህ ሆኖ የሚቀጥል ከሆነ ፖሬቶዜን ትቀጥሳላችሁ ወይስ ታቋርጣላችሁ?

ዛሬ ቅዳሜ እና ነገ እሁድ ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት ጠበቃን ከተጠርጣሪዎች ጋር በሚያገናኙበት ረቡዕ እና አርብ ሄደን አሁንም የምንከከከል ከሆነ እኛ የያገከው አቋም በተጣዩ ተጠር ለፍርድ ቤት አሳስበን ሂደቱ ሕጋዊና ፍትሐዊ ስላልሆነ አንደኛ አስከሁን ስምን ተከሳዩልን በሚለው ጉዳይ ላይ የሚመለከተው የፖሊስ ኃላፊ በአከል ቀርቦ እንዲያስረዳ፣ ሁለተኛ ከዚህ በኋላ በአንዲህ ዓይነት ሁኔታ ታስረው መቆየታቸው ስበለጠ ጉዳት የሚዳርግና በግልም ተጠርጣሪዎቹን የሚጎዳ በመሆኑ የሕግ የበላይነት ላይም ትልቅ ትዕዛና የሚያደርግ በመሆኑ ያለትድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እንዲደረግ፣ ምናልባት ይሄ የማይሆን ከሆነና ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ የሚጠይቅ ከሆነ በሚሰጠው የጊዜ ቀጠሮ ውስጥ ደንበኞቻችንን ማግኘት እንደምንችል ዋስትና ካሳገኘን የእኛ እዚያ መቆየት እንድም ለታሰሩት ልጆች የሚጠቅም ነገር ስለሌለው በዚህ ፍትሐዊ ባልሆነ ሂደት ውስጥ ተባባሪ ሆኖ የመቀጠል ስሜት ስለሚፈጥርብን በእኛ በኩል ራሳችንን ከሂደቱ እናገልላለን። ■